የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.31
ADDIS ABABA 1st April, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፰/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ……………………………………ገጽ ፲፪ሺ፬፻፴፬

## Content

Proclamation No.1178/2020

Prevention and Suppression of Trafficking in Persons and Smuggling of Persons Proclamation No. ……………………………………..…....Page 12,434

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፰/፪ሺ፲፪

### በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

በሰው የመነገድ፣ ሰውን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር እና በህገ-ወጥ መንገድ ለስራ ወደ ውጭ አገር መላክ ወንጀሎች በዜጎች አካል፣ ህይወት እና ደህንነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ እና ለሰብዓዊ መብት ጥሰት እያጋለጡ የሚገኙ ወንጀሎች መሆናቸውን በመገንዘብ ፤

በሰው የመነገድ እና ሰውን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፱/፪ሺ፯ ግልፅነት የሚጎድለው፣ ከሌሎች ህጎች ጋር የማይጣጣምና ለችግሩ በቂ ምላሽ የማይሰጥ ሆኖ በመገኘቱ በአዲስና በተሟላ የሕግ ማዕቀፍ መተካት በማስፈለጉ፤

### PROCLAMATION NO. 1178/2020

### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE PREVENTION AND SUPPRESSION OF TRAFFICKING IN PERSONS AND THE SUMGGLING OF PERSONS

WHEREAS, trafficking in persons, the smuggling of persons and illegal oversea employment crimes are causing serious harm to physical, life and safety of citizens and exposing to grave violations of human rights;

WHEREAS, a Proclamation promulgated for the Prevention and Suppression of Trafficking in Persons and Smuggling of Migrants No. 909/2015 lacks clarity, inconsistent with other laws and does not provide adequate responses to the problem; thereby necessitated for replacement with a new and comprehensive legal framework;



www.chilot.me

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ ፲፰ መሰረት በማንኛውም መንገድ በሰው መነገድ በመከልከሉ እንዲሁም በሰው የመነገድ በተለይም በሴቶችና ሕጻናት መነገድን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ወንጀል ፈፃሚዎችን ለመቅጣት እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ በየብስ፣ በባህርና በአየር ማስወጣትና ማስገባት ለመከላከል የሚያስችሉ ፕሮቶኮሎችን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በማውጣቱና ኢትዮጵያም ስምምነቱን ያፀደቀች በመሆኑ የማስፈጸሚያ ዝርዝር ህግ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

መንግስት ሰዎች በተፈጥሮ እና በህግ የተጎናጸፉትን መብትና ጥቅም የማክበር እና የማስከበር ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ በወንጀል መከላከል፣ ወንጀል ፈፃሚዎችን በህግ ተጠያቂ ማድረግ፣ የተጎጂዎች ጥበቃና መልሶ ማቋቋም በተለይም ለወንጀሎቹ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰቡ ክፍሎችን ተደራሽ የሚያደርግና የተጎጂዎችን ዕድሜ፣ ጾታና ልዩ ፍላጎት ያማከለ ተግባር መፈፀም እና ዓለም አቀፍ ትብብርን ለማጠናከር የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ማውጣት እና ሥርዓት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፭) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፰/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

WHEREAS, in accordance with Article 18 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia prohibits trafficking in human in any manner; as well as Ethiopia, have ratified the protocol to Prevent, Suppress and Punish Trafficking in Persons especially Women and Children and the Protocol Against the Smuggling of Migrants by Land, Sea and Air issued by the United Nations; necessitated enactment of detailed law for the implementation;

RECOGNIZING, the duty of the government to respect and protect rights and benefits persons conferred by nature and law; necessitated enacting legal framework and creating a system that enable crime prevention, holding perpetrator accountable, protecting and rehabilitating victims specially to undertake activities that reaches section of the society vulnerable to the crimes and in taking into consideration the age, sex and special needs of the victims and facilitating international cooperation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (5) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Prevention and Suppression of Trafficking in Persons and Smuggling of Persons Proclamation No. 1178/2020".

www.chilot.me

## ፪. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"የተደራጀ የወንጀል ቡድን"** ማለት በዚህ አዋጅ የተመለከተ ወንጀልን ለመፈጸም ሦስት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰውን የያዘ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በሌላ አገር የሚገኝ ወይም የሚንቀሳቀስ፤ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የሚቆይ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የገንዘብ ወይም ሌላ ማንኛውንም ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት የተዋቀረ ቡድን ነው፤

፪/ **"ባርነት"** ማለት የሌላ ሰው የባለቤትነት መብት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እየተፈፀመበት ያለ ሰው የሚገኝበት ሁኔታ ወይም አቋም ነው፤

፫/ **"አገልጋይ ማድረግ"** ማለት አንድ ሰው ሊያስቀረው፣ ሊከላከለው ወይም ሊቀይረው በማይችልበት ሁኔታ አገልግሎት እንዲሰጥ ወይም ሥራ እንዲሰራ ማድረግ ወይም ማስገደድ ነው፤

፬/ **"በዝሙት አዳሪነትና መሰል የወሲብ ተግባር ብዝበዛ"** ማለት አንድን ሰው ለዝሙት አገልግሎት ማሰማራት፣ ለግብረ ስጋ ግንኙነት አገልግሎት ማቅረብ ወይም መጠቀም ወይም ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ የሆኑ ተግባራት በተለይም ገላን ወይም ሀፍረተ ሥጋ ለሌሎች እንዲያሳይ ማድረግ ሲሆን፤ እነዚህን ተግባራት በፎቶግራፍ፣ በቪዲዮ፣ በድምፅ ወይም በሌላ ማንኛውም መንገድ መቅረጽና ማሰራጨት ወይም ለማሰራጨት ዓላማ መቅረጽን ያካትታል፡፡

## 2. Definitions

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ **"Organized criminal group"** means a structured group of three or more persons living and operating in Ethiopia or elsewhere, existing for a limited or unlimited period of time and acting in concert with the aim of committing one or more offences stipulated under this Proclamation, in order to obtain, directly or indirectly a financial or other material benefit;

2/ **"Slavery"** means the status or condition of a person over whom any or all the powers attaching to the right of ownership are exercised;

3/ **"Servitude"** means the conditions or the obligations to work or to render services from which the person cannot escape, prevent or alter;

4/ **"Sexual or other forms of sexual activities"** means pimping out, using or deploying a person for prostitution, or causing a person to engage in immoral acts, especially by exhibiting one's nakedness or sexual parts for the view of others, including the recording of these acts through the use of a photograph, video, audio or any other means for the purpose of distribution;

www.chilot.me

፭/ **"የህጻናት የጉልበት ብዝበዛ"** ማለት ህፃንን በህግ ከተፈቀደው ሁኔታ ውጭ ወይም ለህጻኑ አካል ወይም ዕድሜ በተጻረረ መልኩ ስራ እንዲሰራ ወይም አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ ነው፤

፮/ **"ከባድ አካል ጉዳት"** ማለት በወንጀል ህግ አንቀጽ ፭፻፶፭ ስር የተመለከተው ሁኔታ ነው፤

፯/ **"ተጎጂ"** ማለት በዚህ አዋጅ ከተመለከቱት የወንጀል ድርጊቶች አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የተፈጸመበት እና አካላዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የደረሰበት ወይም የመብት ጥሰት የተፈጸመበት ወይም እነዚህ ጉዳቶች የደረሱበት ወይም የመብት ጥሰት የተፈጸመበት ባይሆንም ለወንጀሉ የተጋለጠ ወይም ሊጋለጥ የሚችል በመሆኑ በዚህ አዋጅ የተመለከተው ጥበቃ እና ድጋፍ እንደ አግባብነቱ የሚያስፈልገው ሰው ነው፤

፰/ **"ከወንጀል ጋር የተገናኘ ንብረት"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫፣ ፬፣ ፰፣ ፱፣ ፲ ወይም ፲፩ የተመለከተ ወንጀል መፈፀሚያነት የዋለ ንብረት፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በእነዚህ ወንጀል የተገኘ ንብረት፣ ከእነዚህ ወንጀል በተገኘው ንብረት የተፈራው ንብረት ወይም ለእነዚህ ወንጀል መፈፀሚያነት የዋለው ወይም ውጤት የሆነው ወይም የተፈራው ንብረት ያልተገኘ እንደሆነ ተመጣጣኝ ግምት ያለው የወንጀል ፈፃሚውን ንብረት ያጠቃልላል፤

፱/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ፵፯ (፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የአዲስ አበባንና የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

5/ **"Labor exploitation of children"** means causing a child to work or provide a service in a manner other than those permitted by law or contrary to the age or physical strength of the child;

6/ **"Grave physical injury"** means the situation described under Article 555 of the Criminal Code;

7/ **"Victim"** means a person subjected to one or more of the criminal offences stipulated under this Proclamation and having suffered physical, psychological or economic harm, or violation of rights; or though not suffered from such harm or not subject to such violation for the purpose of providing protection and support provided under this proclamation includes person vulnerable or exposed to the crime;

8/ **"Property associated with the crime"** means property used in the commission of crime provided under Article 3, 4, 8, 9, 10 or 11 of this Proclamation, direct or indirect proceeds of the crime, property produced from proceeds of the crime, and includes, when the property obtained through these conditions is not found, equivalent property of the offender;

9/ **"Region"** means any state referred to under Article 47 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, and for the purpose of this Proclamation, it includes Addis Ababa and Dire Dawa City Administration;

www.chilot.me

፲/ **"ሕጻን"** ማለት ዕድሜው ከ፲፰ ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው፤

፲፩/ **"የወንጀል ህግ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር ፬፻፲፬/፲፱፻፺፯ ዓ.ም የወጣው የ፲፱፻፺፯ ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ነው፤

፲፪/ **"ፖሊስ"** ማለት የፌደራል ፖሊስ ወይም በፌደራል ፖሊስ ውክልና የተሰጠው የክልል ፖሊስ ነው፤

፲፫/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፬/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር፣ ህገ ወጥ የውጭ ሀገር የሥራ ሥምሪት ወንጀሎች እና ተያያዥ ወንጀሎች

### ንዑስ ክፍል አንድ

### በሰው የመነገድ ወንጀል

**፫. በሰው የመነገድ ድርጊት**

፩/ ማንኛውም ሰው ሌላውን ሰው በባርነት ወይም በባርነት መሰል ተግባር፣ በአገልጋይነት ወይም ዕዳ መያዣነት የያዘው፤ አካሉን በማውጣት ወይም በዝሙት አዳሪነት ወይም መሰል የወሲብ ተግባር ብዝበዛ የፈፀመበት፤ በግዳጅ ሥራ ወይም አገልግሎት፣ በልመና፣ በወንጀል ተግባር፣ በግዳጅ ጋብቻ፣ ወይም በማህፀን ኪራይ ያሰማራ ወይም ህጻናትን በጉልበት ሥራ የበዘበዘ ወይም እነዚህን መሰል የብዝበዛ ተግባራት የፈፀመ እንደሆነ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሃያ ሺህ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

10/ **"Child"** means any person under the age of 18 years;

11/ **"Criminal Code"** means the Criminal Code of the Federal Democratic Republic of Ethiopia 2004 promulgated with Proclamation No. 414/2004;

12/ **"Police"** means Federal Police or Regional State Police to whom the power of Federal Police is delegated with respect to this Proclamation;

13/ **"Person"** means any natural or juridical person;

14/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO

## TRAFFICKING IN PERSONS, SMUGGLING OF PERSONS, UNLAWFUL SENDING OF PERSON ABROAD FOR WORK AND RELATED CRIMES

### SECTION ONE

### TRAFFICKING IN PERSONS

**3. Act of Trafficking in Persons**

1/ Any person who holds another person in slavery or practices similar to slavery, servitude or debt bondages; exploited in removing organs or prostitution or other forms of sexual activities of another person; engages another person in forced labor or service, begging or criminal act, forced marriage, surrogacy, or exploited children in labor, or commit exploitation similar to these acts shall be punishable with Seven years to Fifteen years of rigorous imprisonment and fine from Twenty Thousand to One Hundred Thousand Birr.

www.chilot.me

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ በተፈፀመው ወንጀል ሂደት ውስጥ ባለፈ ሰውላይ ብዝበዛው የተፈፀመ ወይም መፈፀሙ ተጀምሮ እንደሆነ በሂደቱ የተሳተፈ እንዲሁም ብዝበዛውን የፈፀመው ሰው ከሰባት እስከ አስራ ሁለት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአርባ ሺህ ብር እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) ላይ የተጠቀሱት መንገዶች ጥቅም ላይ ባይውሉም ህጻናትን ለብዝበዛ ዓላማ መመልመል፣ ማጓጓዝ፣ ወደ ሌላ ሰው ማስተላፍ፣ ማስጠለል፣ መደበቅ ወይም መቀበል በሰው የመነገድ ድርጊት ነው፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ከተጠቀሱት መንገዶች ውስጥ አንዱ ያለ እንደሆነ ተጎጂው ብዝበዛው የሚፈፀምበት መሆኑን ማወቁ ወይም መስማማቱ የድርጊቱን ፈፃሚ ከወንጀል ተጠያቂነት የሚያስቀር አይሆንም፡

፭/ ለዚህ ንዑስ ክፍል አፈጻጸም "የተጠቀሱት መንገዶች" ማለት ኃይል መጠቀም፣ ማገት፣ መጥለፍ፣ ማስፈራራት ወይም ሌላ የማስገደጃ ዘዴ መጠቀም፣ ማታለል፣ የተስፋ ቃል መስጠት፣ ሥልጣንን አላግባብ መጠቀም፣ የሰውን ተጋላጭነት መጠቀም ወይም ስለሌላው ኃላፊነት ያለበትን ሰው ፈቃድ ለማግኘት መደለያ ወይም ጥቅም መስጠት ወይም መቀበል ነው፡፡

## ፬. ከባድ ሁኔታ

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ (፩) ወይም (፪) ላይ የተመለከተው የወንጀል ድርጊት የተፈጸመው፡-

ሀ) በሕጻናት፣ በአዕምሮ ህመምተኛ ወይም በአካል ጉዳተኛ ላይ ከሆነ፤

2/ A person who pass through a criminal process stipulated under Sub-Article (1) of this Article, whether the exploitation is started or completed, the perpetrator as well as his collaborates shall be punishable with rigorous imprisonment from Seven years to Twelve years and with fine from Forty Thousand to One Hundred Thousand Birr.

3/ The recruitment, transportation, transferring, harboring, hiding or receipt of a child for the purpose of exploitation shall be considered "trafficking in persons" even if this does not involve any of the means mentioned in Sub-article (2) of this Article;

4/ If the means mentioned under Sub-Article (2) of this Article have been used, the fact that the victim is consented or have the knowledge to the exploitation shall not relief the perpetrator from criminal liability.

5/ For the purpose of this sub-section `means mentioned` means threat or use of force or other means of coercion, or abduction, fraud, of deception, abuse of power or of a position of vulnerability, or by the giving or receiving of payments or benefits to achieve the consent of a person having control over the person.

## 4. Aggravating Circumstances

1/ Where the crime stipulated under Article 3(1) or (2) of this Proclamation is committed:-

a) against a child or mentally ill or physically disabled;

www.chilot.me

ለ) አደንዛዥ ዕፅ፣ መድሃኒት ወይም የጦር መሣሪያ በመጠቀም እንደሆነ፤

ሐ) በመንግስት ሠራተኛ ወይም በባለሥልጣን ከሆነና ወንጀሉን የፈፀመው የተሰጠውን ኃላፊነት መከታ በማድረግ ከሆነ፤ ወይም

መ) የአገር ውስጥ ወይም የውጭ አገር የሥራ ስምሪት ፈቃድ ባለው አካል ፈቃዱን ሽፋን በማድረግ እንደሆነ፤

ከአስር ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሰላሳ ሺህ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ (፩) ወይም (፪) የተመለከተው የወንጀል ድርጊት፡-

ሀ) የተደራጀ የወንጀል ቡድን አባል በመሆን ወይም ቡድኑን በመምራት ወይም በማስተባበር የተፈፀመ፤

ለ) በተጎጂው ላይ የማይድን በሽታ ያስከተለ፤ ወይም

ሐ) የተጎጂው ሕይወት ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የወደቀ ወይም በተጎጂው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት የደረሰበት ወይም ለኢ-ሰብዓዊ አያያዝ የተዳረገ እንደሆነ፤

ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሃምሳ ሺህ እስከ አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

መ) በተጎጂው ላይ ሞት አስከትሎ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ወይም ዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት እና ከሃምሳ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

b) by using drugs, medicine or weapons;

c) by a public official or civil servant and the person committed the offence by abusing the powers entrusted to him; or

d) by an organization licensed to conduct domestic or foreign employment services by abusing its license;

the punishment shall be rigorous imprisonment from Ten years to Twenty years and a fine from Thirty Thousand to One Hundred Thousand Birr.

2/ Where the crime stipulated under Article 3 (1) or (2) of this Proclamation:-

a) was committed being a member, a leader or coordinator of an organized criminal group;

b) resulted chronic disease on the victim; or

c) Endangered the life or safety of the victim or caused grave bodily injury to the victim or subjected for inhuman treatment;

the punishment shall be rigorous imprisonment of Fifteen years to Twenty-Five years and with fine from Fifty Thousand Birr to Two Hundred Thousand Birr.

d) Where the offence causes the death of the victim, depending on the circumstances of the case, the punishment shall be rigorous imprisonment from Fifteen years to Twenty Five years or life

www.chilot.me

፫/ የተፈጸመው ድርጊት የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ በሚሆንበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል (ሀ) ህጻናት የሚለው ማክበጃ ምክንያት በማክበጃነት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## ፭. በሰው የመነገድ ድርጊትን መደገፍ

በወንጀል ሕጉ ስለአባሪነት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም ሰው በሰው ለመነገድ ዓላማ መጠቀሚያ መሆኑን እያወቀ ፡-

፩/ የራሱንም ሆነ በይዞታው ስር የሚገኝ ቤት፣ ህንጻ ወይም ግቢ ያከራየ ወይም እንዲጠቀሙበት የፈቀደ፤ ወይም የትራንስፖርት አገልግሎት የሰጠ ወይም ተጎጅዎችን ያጓጓዘ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአስር ሺህ እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ የተጭበረበረ፣ ሀሰተኛ ወይም በሕገወጥ መንገድ መታወቂያ ወይም የጉዞ ሰነድ ያዘጋጀ፣ የሰጠ፣ ያቀረበ ወይም ይዞ የተገኘ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና ከአስር ሺህ እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ፮. የብዝበዛ ዓላማን ስለመገመት

አንድ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ (፪) ከተጠቀሱት መንገዶች አንዱን በመጠቀም ሰውን የመመልመል፣ የማጓጓዙ፣ ወደ ሌላ ሰው የማስተላለፉ፣ የማስጠለል፣ የመደበቅ ወይም የመቀበል ተግባራት ማከናወኑ ወይም የተጠቀሱት መንገዶች ባይኖሩም እነዚህን ተግባራት በህጻናት ላይ ማከናወኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ይህን ድርጊት ለየትኛው የብዝበዛ ዓላማ እንደተፈጸመ በአከባቢ ማስረጃ ግምት ለመውሰድ ይቻላል፡፡

imprisonment or death and fine from Fifty Thousand to Two Hundred Thousand Birr.

3/ Where the act committed is child labor exploitation, the aggravating circumstance of being against child stated under Sub-Article (1) letter (a) of this Article shall not be applicable for aggravation.

## 5. Assisting the act of Human Trafficking

Without prejudice to provision of the criminal code regarding accomplice, any person knowing that it is to be used for purpose of human trafficking:-

1/ Permit or rent house, building or premises of his own or in his control or provide transport service or transport the victims shall be punishable with rigorous imprisonment from three years to seven years and fine from Ten Thousand to Fifty Thousand Birr.

2/ Produced, give, provide or holds fraudulent, falsified or illegal identity card or travel document shall be punishable with rigorous imprisonment from five years to fifteen years and fine from Ten Thousand to Fifty Thousand Birr.

## 6. Presuming Purpose of Exploitation

Where it is proved that a person recruit, transport, transfer, harbor, hide or receive another person using means mentioned under Article 3(2) of this Proclamation; or without using means mentioned commit such act against child; presumption may be made on basis of circumstantial evidence for which exploitation purpose the person committed such act.

www.chilot.me

**፯. <u>በሌሎች የዝሙት አዳሪነት መጠቀም</u>**

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ እና ፬ ከተመለከተው ሁኔታ ውጭ ሌሎች ሰዎች ከሚፈጽሙት የዝሙት አዳሪነት ተግባር ወይም የሥነ-ምግባር ብልሹነት ለመጠቀም ሲል ወይም የሌላውን ሰው ፍትወተ ስጋ ፍላጎት ለማርካት በማሰብ ሌላውን ሰው ለዝሙት ተግባር ያሰማራ፣ ያገናኘ፣ ያቀረበ፣ በዝሙት አዳሪ ቤት ያስቀመጠ፣ የሥራ ወይም የመኖሪያ ቤቱን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለዚህ ተግባር ያዋለ ወይም ያከራየ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የሌላውን ሰው የዝሙት ድርጊት ወይም የሥነ-ምግባር ብልሹነት መጠቀሚያ አድርጎ የያዘ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአስር ሺህ እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>**

**<u>ሰውን በህገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል</u>**

**፰. <u>በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር</u>**

፩/ ማንኛዉም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የገንዘብ ወይም ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ሰዉን በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት እንዲገባ፣ ከኢትዮጲያ ግዛት እንዲወጣ፣ በኢትዮጵያ ግዛት እንዲተላለፍ ያደረገ ወይም ሰውን ከኢትዮጵያ ግዛት ለማስወጣት ዝግጅት ያደረገ፣ በሂደት ላይ የተገኘ፣ ያጓጓዘ ወይም የተቀበለ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና ከአስር ሺህ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው የወንጀል ድርጊት የተፈጸመው፡-

ሀ) በሕጻናት፣ በአዕምሮ ህመምተኛ ወይም በአካል ጉዳተኞች ላይ ከሆነ፣

**7. <u>Exploitation of the Prostitution of Others</u>**

Apart from the circumstances stipulated under Articles 3 and 4 of this Proclamation, any person for the purpose of benefiting from the prostitution or immorality of another or to gratify the sexual passions of another, causes another to engage in prostitution, acts as go between, procures, keeps in a brothel, uses or rents out his residence or place of business for this purpose in whole or in part or uses the prostitution or immorality of another in any other manner shall be punishable with rigorous imprisonment from one year to five years and fine from Ten Thousand to Fifty Thousand Birr.

**<u>SUB-SECTION TWO</u>**

**<u>CRIME OF SMUGGLING OF PERSONS</u>**

**8. <u>Smuggling</u>**

1/ Any person who, for direct or indirect financial or material gain for himself or for another person, enables a person to illegally enter into the territory of Ethiopia, exit the territory of Ethiopia, transit through the territory of Ethiopia, or to cause exit of another person from Ethiopian territory make preparation, found in the process, transport or receive shall be punishable with rigorous imprisonment from Five years to Ten years and fine from Ten Thousand to One Hundred Thousand Birr.

2/ Where the offence stipulated under Sub-Article (1) of this Article is committed:-

a) against a child, mentally ill or physically disabled;

www.chilot.me

ለ) አደንዛዥ ዕፅ፣ መድሃኒት ወይም የጦር መሣሪያ በመጠቀም ከሆነ፤

ሐ) በመንግስት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ ከሆነ እና ወንጀሉን የፈፀመው የተሰጠውን ኃላፊነት መከታ በማድረግ ከሆነ፤ ወይም

መ) የውጭ አገር የሥራ ስምሪት ፈቃድ ያለው ሰው ፈቃዱን ሽፋን በማድረግ፤

ከሆነ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሃያ ሺህ እስከ አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከተው የወንጀል ድርጊት፡-

ሀ) በተጎጂው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት፣ የማይድን በሽታ ወይም ዘላቂ የአዕምሮ ጉዳት ያስከተለ፤

ለ) ወንጀል አድራጊው ድርጊቱን የፈፀመው የተደራጀ የወንጀል ቡድን አባል በመሆን፣ ቡድኑን በመምራት ወይም በማስተባበር፤ ወይም

ሐ) የተጎጂው ህይወት ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የወደቀ ወይም ኢ-ሰብአዊ ለሆነ አያያዝ የተዳረገ፤

እንደሆነ ከአስር ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሰላሣ ሺህ እስከ አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

መ) በተጎጂው ላይ ሞትን ያስከተለ እንደሆነ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ወይም የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም ሞት እና ከሃምሳ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

b) by using drugs, medicine or weapons;

c) by a public official or civil servant and the person committed the offence by abusing the powers entrusted to him; or

d) by an organization licensed to engage in foreign employment services by abusing its license;

the punishment shall be rigorous imprisonment of seven years to fifteen years and fine from Twenty Thousand to One Hundred Thousand Birr.

3/ Where the offence stipulated under Sub-Article 1 of this Article:-

a) resulted in grave bodily injury or chronic disease or permanent mental disorder on the victim;

b) committed by an offender being a member, a leader or coordinator of an organized criminal group; or

c) Endangered the life or safety of the victim or the victim subjected for inhuman treatment;

the punishment shall be rigorous imprisonment of ten years to twenty years and with fine from Thirty Thousand to One Hundred Fifty Thousand Birr.

d) has resulted in the death of the victim, depending on the circumstances of the case, the punishment shall be rigorous imprisonment from Fifteen years to Twenty Five years or life imprisonment or death and fine from Fifty Thousand to Two Hundred Thousand Birr.

www.chilot.me

## ፱. <u>በህገ-ወጥ መንገድ መቆየትን ስለመርዳት</u>

፩/ ማንኛውም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የገንዘብ ወይም ቁሳዊ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ወይም ለመቆየት የሚያስችል የፀና ፈቃድ የሌለውን ሰው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንዲቆይ ሀሰተኛ ሰነድ በመስራት፣ በማቅረብ ወይም በሌላ ማንኛውም ህገ-ወጥ መንገድ የረዳ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአስር ሺህ እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ድርጊት የተፈፀመው ጥቅም ለማግኘት ያልሆነ እንደሆነ አግባብነት ያለው የወንጀል ህግ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ፲. <u>በህገወጥ መንገድ ድንበር ለመሻገር መፈፀሚያነት ስለሚውል ሰነድ</u>

ማንኛውም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ሰዉን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር ለማሻገር ወንጀል መፈፀሚያነት እንዲዉል ሀሰተኛ የጉዞ ወይም የማንነት መታወቂያ ሰነድ ያዘጋጀ፣ ይዞ የተገኘ፣ ያቀረበ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ አስራት እና ከአስር ሺህ እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሶስት</u>
## <u>የውጭ ሀገር የስራ ስምሪት ወንጀል</u>

## ፲፩. <u>በህገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለሥራ ወደ ውጭ አገር መላክ</u>

## 9. <u>Assisting Illegal Stay</u>

1/ Whosoever, for direct or indirect financial or material gain for himself or for another person, assists a foreigner to stay or live in Ethiopia knowing that the foreigner does not have a valid residence permit by producing or procuring forged documents, or in any other illegal manner is punishable with rigorous imprisonment of from five years to ten years and fine from Ten Thousand to Fifty Thousand Birr.

2/ Where the offence stipulated under Sub-Article (1) of this Article was not committed for gain, the appropriate provisions of criminal law shall be applicable.

## 10. <u>Documents used to Smuggle</u>

Whosoever, for direct or indirect financial or material gain for himself or for another person, prepares, is found in possession of, provide or transfers forged or a falsified travel document or identity card for use in the commission of smuggling of persons shall be punishable with rigorous imprisonment of five years to fifteen years and fine from Ten Thousand to Fifty Thousand Birr.

## <u>SECTION THREE</u>
## <u>CRIMES OF OVER SEA EMPLOYMEENT</u>

## 11. <u>Unlawful Sending of Person Abroad for Work</u>

www.chilot.me

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ እና ፰ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጪ፡-

፩/ ማንኛውም ሰው ወደ ውጭ አገር ሰውን ለሥራ ለመላክ ፈቃድ ሳይኖረው፣ ፈቃዱ ታግዶ ወይም ተሰርዞ እያለ ወይም እንዲልክ ፈቃድ ወዳልተሰጠው አገር ሰውን ለሥራ የላከ እንደሆነ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ ሁለት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና ከሃያ ሺህ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው የጉብኝት፣ የህክምና፣ የትምህርት ወይም የመሰል ጉዳዮች ቪዛን ሽፋን በማድረግ እንደሆነ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሰላሳ ሺህ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) በተመለከተው የወንጀል ድርጊት ምክንያት የተላከው ሰው በሰብዓዊ መብቱ፣ በህይወቱ፣ በአካሉ ወይም በሥነ-ልቦናው ላይ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ የላከው ሰው ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ወይም በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት እና ከሃምሳ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ፲፪. የውጭ አገር ስራ ስምሪት አገልግሎት ጋር በተያያዘ ስለሚፈፀም ወንጀል

ማንኛውም የውጭ አገር ሥራና ሰራተኛ ማገናኘት ፈቃድ ያለው ሰው የሥራ ስምሪት አገልግሎቱን ምክንያት በማድረግ ከሰራተኛ ገንዘብ ወይም ቁስ የተቀበለ፣ የሠራተኛውን መታወቂያ፣ ፓስፖርት፣ የጉዞ ሰነድ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰነድ ሰራተኛው ወደ ሥራ ከመሰማራቱ በፊትም ሆነ በኋላ

Apart from the circumstances stipulated under Article 3 and 8 of this Proclamation፡-

1/ Any person who sends person abroad for work without having obtained a license or while the license has been suspended or canceled or send to a country which permission is not granted under the license is punishable with rigorous imprisonment from seven years to twelve years and fine from Twenty Thousand to One Hundred Thousand Birr.

2/ Where the crime stipulated under Sub-Article 1 of this Article is committed with the pretext of visit, medical, educational or similar visas; the punishment shall be rigorous imprisonment from seven years to fifteen years and fine from Thirty Thousand to One Hundred Thousand Birr.

3/ Where the person sent abroad, owing to the act stipulated under Sub-Article (1) or (2) of this Article, suffers harm to his human rights, life, body or psychological makeup, the sender shall be punished with rigorous imprisonment from fifteen years to twenty-five years or life imprisonment and with fine from Fifty Thousand to Two Hundred Thousand Birr.

## 12. Offences Committed in Connection with Overseas Employment Services

Whosoever having a license to provide oversea employment services receives money or materials from the worker in consideration of the employment services; withholds or refuses identity card, passport, travel documents or any other document of the worker without his

www.chilot.me

ያለሰራተኛው ፈቃድ የያዘ ወይም የከለከለ፤ በማታለል ወይም በማንኛውም የማስገደጃ መንገድ ሰራተኛው ባለመብት የሆነበትን ጥቅም እንዲተው ያደረገ ፤ ወይም የሰራተኛውን ደመወዝ፣ ንብረት ወይም ሰራተኛው የሚልከውን ገንዘብ በሰራተኛው ፈቃድም ቢሆን እንኳን የያዘ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከሰላሳ ሺህ እስከ ሰባ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ንዑስ ክፍል አራት
## ተያያዥ ወንጀሎች

### ፲፫. ወንጀልን አለማስታወቅ

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫፣ ፬፣ ፰ ወይም ፲፩ ሥር የተመለከተው ወንጀል መፈፀሙን ወይም እየተፈጸመ መሆኑን ወይም የወንጀሉን ፈፃሚ ማንነት እያወቀ በቂ ምክንያት ሳይኖረው ለፖሊስ ወይም አግባብነት ላለው የህግ አስከባሪ አካል ወዲያውኑ ያላሳወቀ ወይም ሐሰተኛ ማስረጃ የሰጠ እንደሆነ ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ይቀጣል፤ ድርጊቱ ከባድ ሲሆን ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

### ፲፬. በጠቋሚዎች እና በምስክሮች ላይ የሚፈፀም ወንጀል

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በተመለከተ ወንጀል ጠቋሚ ወይም ምስክር ሊሆን የሚችል ወይም ማስረጃ ያለው ሰው፤ መረጃውን ወይም ማስረጃውን ለፍትሕ አካላት እንዳይሰጥ ወይም በምርመራ ወይም በክርክር ሂደት ምስክር ሆኖ እንዳይቀርብ በእርሱ ወይም ከእርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት ባለው ሰው ላይ የተንኮል፣ የኃይል ስራ፣ የማስፈራራት፣ የማይገባ ጥቅም

consent either before or after the worker engaged in work; causes the worker to abandoned benefits he is entitled to through deceit or other means, or withholds, even with permission of the worker, the salary or property of the worker or monies transferred by the worker shall be punishable considering the circumstances of the case with rigorous imprisonment from three years to seven years and fine from Thirty Thousand to Seventy Thousand Birr.

## SUB-SECTION FOUR
## RELATED CRIMES

### 13. Failure to Report the Commission of an Offence

Whosoever without justifiable cause fails to report immediately to the police or appropriate law enforcement organ knowing that any act provided for in Articles 3,4, 8, or 11 of this Proclamation is committed or being committed or knowing the identity of the suspect or provides false information shall be punishable with not less than three months simple imprisonment; where the act is grave the punishment shall be rigorous imprisonment from one year to five years.

### 14. Offence Against Whistle Blowers or Witnesses

1/ Whosoever interferes to prevent a person who may be whistleblower or witness or who has evidence of crime provided under this Proclamation from giving information or evidence to justice authorities or being a witness in an investigation or judicial proceeding by using sabotage, violence, threat or by extending undue advantage, by

www.chilot.me

በመስጠት ወይም በመደለል፣ ወይም በሌላ ማንኛውም መንገድ ጣልቃ በመግባት የከለከለ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከተ ወንጀልን አስመልክቶ ጥቆማ ወይም መረጃ የሰጠን፣ ወይም ምስክር ሆኖ የቀረበን ሰው መረጃ በመስጠቱ ወይም ምስክር ሆኖ በመቅረቡ ምክንያት፤ በእርሱ ላይ ወይም ከእርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት ባለው ሰው ላይ ጥቃት፣ ማስፈራራት፣ ወይም ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተመለከተው ወንጀል በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የጤና ጉዳትን ወይም ሞትን አስከትሎ እንደሆነ፤ እነዚህን ወንጀሎች በሚመለከት አግባብነት ያላቸው ህጎች በተደራቢነት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**፲፭. ማስረጃን ስለማጥፋት**

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በተመለከተ ወንጀል በምርመራ ወይም በፍርድ ክርክር ሂደት ላይ ሊቀርብ የሚችልን ማስረጃ ሆን ብሎ ያጠፋ፣ ያበላሸ ወይም የደበቀ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ተግባር አፈጻጸም ከባድ በሆነ ጊዜ በተለይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫፣ ፬፣ ፰ ወይም ፲፩ የተመለከቱ ድርጊቶችን ለማስረዳት የሚውል እና የዋና ማስረጃ ይዘት ያለው እንደሆነ ቅጣቱ ከሶስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይሆናል፡፡

inducements or getting involved in any other way against such person or a person who has close relationship with him shall be punished with rigorous imprisonment from three years to seven years.

2/ Whosoever assaults, threats, or causes harms to any person or a person who has close relationship with such person, for the fact he gave information or evidence to justice authorities or appeared as witness in an investigation or judicial proceeding of crime provided for in this Proclamation shall be punishable with rigorous imprisonment from three years to seven years.

3/ Where the crime mentioned in Sub-Article (1) or (2) of this Article entailed grave harm to the body or health of the victim or his death, the relevant laws related to these crimes shall apply concurrently.

**15. Destroying Evidence**

1/ Whosoever destroys, damage, or hide intentionally any evidence to be used in the course of investigation or judicial proceedings of crime provided under this Proclamation shall be punishable with one year to three years rigorous imprisonment.

2/ Where the acts provided for under Sub-Article (1) of this Article committed in grave manner or where the evidence considered as substantial in the investigation or judicial proceeding of terrorism crime and to be used to prove acts provided under article 3, 4, 8 or 11 of

www.chilot.me

፫/ የወንጀል ምርመራውን፣ የክርክሩን ወይም የፍርድ ሂደቱን ማከናወን የተቻለ ወይም ተከሳሽ በወንጀሉ ጥፋተኛ የተባለ ቢሆንም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ፲፮. ተጠርጣሪን እንዳይከሰስ ስለመርዳት

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫፣ ፬፣ ፭፣ ፰፣ ፱፣ ፲ ወይም ፲፩ በተመለከተ ድርጊት የተጠረጠረን ወይም የተከሰሰን ሰው አስቀድሞ በማስጠንቀቅም ሆነ በመደበቅ፣ ዱካውን በመሸሸግ ወይም በማጥፋት፣ የሚደረግ ምርመራን በማሳሳት ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ተከሶ እንዳይቀርብ የረዳ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ድርጊት የፈፀመ ሰው የተከሳሽ መያዝ ወይም መከሰስ ወይም ምርመራው በአግባቡ መከናወንና መጠናቀቅ ከተጠያቂነት ነፃ አያደርገውም፡፡

## ፲፯. ንብረት ስለመሰወር

፩/ ማንኛውም ሰው ከወንጀል ጋር የተገናኘ ንብረትን እንዳይወረስ ለማድረግ በማሰብ የደበቀ፣ ጉዳት ያደረሰበት ወይም በማናቸውም መልኩ እንዳይታወቅ ያደረገ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከአስር ሺህ እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

this Proclamation the punishment shall be rigorous imprisonment from three years to ten years.

3/ The provisions of Sub-Article (1) and (2) of this Article shall be applicable even where the investigation, trial or judgment has proceeded, or the accused has been found guilty of the offence.

## 16. Aiding Suspect not to be Prosecuted

1/ Whosoever knowingly saves from prosecution, a person who is suspected or accused of committing one of the crimes provided for under Article 3, 4, 5, 8, 9, 10 or 11 of this Proclamation whether by warning or hiding him, by concealing or destroying the traces, by misleading the investigation, or in any other way, shall be punishable with rigorous imprisonment from three years to five years.

2/ The fact that arresting of the suspect or prosecution or successfully conducting and completion of the investigation shall not release from liability the person who has committed the act stipulated under Sub-Article (1) of this Article.

## 17. Concealing Property

1/ Any person with intention of preventing forfeiture concealed, damaged or disguised in any other manner a property associated with the crimes shall be punishable with rigorous imprisonment of three years to seven years and fine of Ten Thousand Birr to Fifty Thousand Birr.

www.chilot.me

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ድርጊቱ የተፈጸመው ንብረቱን ህጋዊ አስመስሎ ለማቅረብ እንደሆነ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፯፻፹/፪ሺ፭ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፲፰. <u>የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት</u>**

፩/ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፺ (፩)፣ (፫) እና (፬) ላይ የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አዋጅ የተደነገገው ወንጀል የተፈፀመው የሕግ ሰውነት በተሰጠው ድርጅት እንደሆነ ለወንጀሉ የሚጣለው ቅጣት፡-

(ሀ) በቀላል እስራት ወይም እስከ ፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ከሆነ እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር

(ለ) ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ከሆነ ከአምስት መቶ ሺህ እስከ አንድ ሚሊዮን ብር፣

(ሐ) ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ከሆነ ከአንድ ሚሊዮን እስከ ሁለት ሚሊዮን ብር፣

(መ) ከሃያ ዓመት በላይ በሆነ እስራት ወይም በሞት ከሆነ ከሁለት ሚሊዮን ብር እስከ ሶስት ሚሊዮን ብር፣

በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተደነገገው ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ በዐቃቤ ህግ ጠያቂነት ወይም በራሱ አነሳሽነት ድርጅቱ እንዲፈርስ ወይም ንብረቱ እንዲወረስ ሊወስን ይችላል፡፡

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, where the act was committed for the purpose of money laundering, the relevant provisions of the Prevention and Suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism Proclamation Number 780/2013 shall be applicable.

**18. <u>Criminal Liability of a Juridical Person</u>**

1/ Notwithstanding Article 90 (1), (3) and (4) of the Criminal Code, where any offence stipulated under this Proclamation is committed by a juridical persons, the penalty shall be a fine:

a) not exceeding Five Hundred Thousand Birr for a crime punishable with simple imprisonment or rigorous imprisonment of up to five years;

b) from Five Hundred Thousand Birr to One Million Birr for a crime punishable with rigorous imprisonment of Five years to Fifteen years;

c) from One Million Birr to Two Million Birr for a crime punishable with rigorous imprisonment of fifteen years to twenty years;

d) from Two Million Birr to Three Million Birr for a crime punishable with rigorous imprisonment exceeding twenty years or with death;

2/ In addition to the punishment stipulated under Sub-Article (1) of this Article, the Court may, at the request of the prosecution or on its own initiative, decide to dissolve the organization or confiscation of its properties.

www.chilot.me

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቅጣት በድርጅቱ ስም ወይም ለድርጅቱ ጥቅም ለማስገኘት በማሰብ በድርጊቱ የተሳተፈውን የድርጅቱን ባለቤት፣ ሥራ አስኪያጅ፣ የድርጅቱን ሠራተኛ ወይም ሌላ ማንኛውንም ሰው የወንጀል ተጠያቂነት አያስቀረውም፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለወንጀል መከላከል እና ንብረት መውረስ

### ፲፱. ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎችን ስለማዳን

፩/ ፖሊስ በሰው የመነገድ ወይም ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል የተፈፀመ፣ እየተፈፀመ ወይም ሊፈፀም የተቃረበ ለመሆኑ በበቂ ምክንያት የጠረጠረ እንደሆነ፡-

ሀ) ማንኛውንም ማጓጓዣ፣ ቤት፣ ስፍራ ወይም ይዞታ በመፈተሽ ለድርጊቱ የተጋለጡ ወይም በድርጊቱ የተጎዱ ሰዎችን ለማዳን ይችላል፤

ለ) ድንበር እያቋረጡ ወይም ድንበር ለማቋረጥ በሂደት ላይ ያሉ ሰዎችን ለማስቆምና ለማጣራት ይችላል፤ ሆኖም የማጣራቱን ተግባር ወዲያውኑ የማከናወን እና ተጎጂ ወይም ተጠርጣሪ ያልሆኑ ሰዎችን ወዲያው የመልቀቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

፪/ ፖሊስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) መሰረት ቤት እና ይዞታን መፈተሽ የሚችለው በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ብቻ ነው፡፡ አስቸኳይ ሁኔታ ሲኖር ፖሊስ ፍተሻውን ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማድረግ የሚችል ሲሆን በሰባ ሁለት ሰዓት ውስጥ ለፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡ ፍርድ ቤቱም አስቸኳይ ሁኔታ የነበረ መሆኑን ጭምር በመመርመር ተገቢ ነው የሚለውን ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

3/ The punishment stipulated under Sub-Article (1) of this Article may not preclude the individual criminal liability of the owner, manager, employee or other person having participated in the commission of the crime on behalf and for the benefit of the organization.

## SECTION THREE
## CRIME PREVENTION, INVESTIGATION AND APPROPRIATION OF PROPERTY

### 19. Protection of Persons Vulnerable to Danger

1/ Where police reasonably suspect that a crime of trafficking in persons or smuggling of persons has been, is being or likely to be committed:-

a) search any of transport, house, location or premises to rescue persons subjected to or harmed by the act;

b) stop and investigate persons crossing or in the process of crossing a border; however, have the duty to conduct the investigation forthwith and release persons who are not victims or suspects.

2/ The police shall conduct search of house or premises under the provisions of Sub-Article (1) (a) of this Article with a court order. Nevertheless, the police may, in urgent situation, conduct a search without a court order, provided that the results of such search shall be presented to the court within seventy-two hours. The court shall issue appropriate orders having examination including existence of urgent situation.

www.chilot.me

፫/ ፖሊስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ተግባር ሲፈጽም ተጎጂዎችን ያገኘ እንደሆነ ተገቢው እንክብካቤና ድጋፍ ወደሚያገኙበት ማዕከል ያደርሳል፡፡

፬/ ፖሊስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ተግባር ሲፈጽም የህመም ስቃይ ወይም ጉዳት ውስጥ የሚገኙ ተጎጂዎች ባጋጠሙት ጊዜ በማናቸውም የመንግስት ወይም የግል የህክምና ተቋም እርዳታ እንዲደረግላቸው ትዕዛዝ ለመስጠት ይችላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) በተገለጸው ተግባር ምክንያት የህክምና አገልግሎት የሰጠ ተቋም ለአገልግሎቱ ወጪ ከፈንዱ የሚከፈለው ይሆናል፤ የአከፋፈሉ ሁኔታ ሥርዓት ስለፈንዱ አስተዳደር በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**፳. <u>ከወንጀል ጋር የተገናኘን ንብረት ስለማገድና መያዝ</u>**

፩/ በሌላ ህግ ስለማይታገዱ እና ስለማይወረሱ ንብረቶች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት፣ በዐቃቤ ህግ ወይም በፖሊስ አመልካችነት በዚህ አዋጅ መሰረት ሊወረስ የሚችል ከወንጀል ጋር የተገናኘ ንብረት ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ የሚያስችሉ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጊዜያዊ እርምጃዎችን ጨምሮ የማገድ ወይም የመያዝ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3/ Where the police discover victims in conducting the measures stipulated under the provisions of Sub-Article (1) of this Article, shall transport the victim to centers where he can receive appropriate care and support.

4/ The police may order any governmental and non-governmental medical institution to avail proper medical treatment to victims suffering serious illness or injury discovered in undertaking the responsibilities under Sub-Article (1) of this Article.

5/ A medical institution having provided services as a result of the action stipulated under Sub-Article (4) of this Article shall be paid from the Fund. The conditions of payment shall be determined by the regulations to be issued on the administration of the Fund.

**20. <u>Freezing and Seizing of Property Associated with a Crime</u>**

1/ Without prejudice to the provisions of other laws dealing with exemption of property from freezing and confiscation, the court may on its own initiative or upon application by the prosecution or the police issue an order, including other temporary measures for the protection of the properties, of freezing or seizure of properties associated with a crime that may be subject to confiscation under the provisions of this Proclamation.

www.chilot.me

፪/ ፖሊስ የወንጀል ክሱ ከመመስረቱ በፊት ወይም ዐቃቤ ህግ የወንጀል ክስ ከተመሰረተ በኋላ ከወንጀል ጋር የተገናኘ ንብረት እንዲታገድ ወይም እንዲያዝ በቃለ መሀላ በተደገፈ ማመልከቻ ፍርድ ቤትን ለመጠየቅ ይችላል፡፡

፫/ ተከሳሹ በሌለበት የእግድ ወይም የመያዙ ትእዛዝ ከተሰጠ ፖሊስ ወይም ዐቃቤ ህግ ትእዛዙንና ቃለ መሀላውን ለተከሳሹ ወይም በንብረቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ ለሚል ሰው ያደርሳል፡፡ ተከሳሽን ማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ በቋሚ አድራሻው ትዕዛዙን ይለጥፋል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የተወሰነን ማንኛውም ጊዜያዊ እርምጃ፣ ውሳኔውን በሰጠው ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት ወይም በዐቃቤ ሕግ፣ በወንጀሉ ተጠርጣሪ ወይም በንብረቱ ላይ መብት አለኝ በሚል ሰው አመልካችነት በማናቸውም ጊዜ ሊነሳ ይችላል፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም አስቸኳይ ሁኔታ ሲኖር የወንጀል ጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ስልጣን ያለው ዐቃቤ ህግ ተቋም ኃላፊ ለሰባ ሁለት ሰዓት የሚፀና ጊዜያዊ የእግድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም ዐቃቤ ህግ ጊዜያዊ እግድ መስጠት ያስፈለገበትን ምክንያት በመግለጽ ሰባ ሁለት ሰዓቱ ከማለፉ በፊት ለፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፣ ፍርድ ቤቱም ተገቢነት ያለውን ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

፮/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም “ማገድ” ማለት በንብረት ላይ በፍርድ ቤት በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ጸንቶ ለሚቆይበት ጊዜ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሰረት ለሰባ ሁለት ሰዓት ወደ ሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ፣ እንዳይለወጥ፣ እንዳይወገድ ወይም እንዳይንቀሳቀስ መከልከል ነው፡፡

2/ The police, prior to the filing of charges, or prosecutor, after the filing of charges, may submit an application supported by affidavit to the court for the freezing or seizure of properties associated with the crime.

3/ Where the order for freezing or seizure has been issued in the absence of the accused, the investigator or prosecutor shall serve the order and affidavit to the accused or other person claiming a right or interest in the property. Where the accused cannot be found, the order shall be served at his permanent address.

4/ The court having issued a temporary order pursuant to Sub-Article (1) of this Article may lift the order at any time by its own initiative or upon application by the prosecutor, the suspect or other person claiming a right to the property.

5/ Notwithstanding the provisions of Sub-Articles (1) of this Article, in urgent situation the head of the relevant prosecution office mandated to make a decision on the criminal case may issue a temporary freezing order valid for a period of seventy-two hours. However, the prosecutor shall submit reasons for freezing the property to the court before the seventy-two hours lapses; the court shall issue the appropriate orders.

6/ For the implementation of this Article, “freezing” shall mean a prohibition on the transfer, conversion, disposition or movement of property by a court order for given duration or for the period of seventy-two hours as per Sub-Article (5) of this Article.

www.chilot.me

፯/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "መያዝ" ማለት በንብረት ላይ ታግዶ ያለ ንብረት በፍርድ ቤት በተሾመና ቁጥጥር በሚደረግበት ንብረት አስተዳዳሪ ስር እንዲተዳደር ማድረግ ነው፡፡

## ፳፩. ንብረት ስለመውረስ

፩/ በዚህ አዋጅ የተመለከተ ወንጀል ጉዳይን ለማየት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት፡-

ሀ) በተከሳሽ ላይ የወንጀል የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) የወንጀሉ ፈጻሚ ባለመታወቁ፣ በመሰወሩ፣ በመሞቱ፣ በተለያየ ምክንያት ምርመራ ወይም ክስ በመቋረጡ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት የጥፋተኝነት ውሳኔ ባይሰጥም ንብረቱ ከወንጀሉ ጋር የተገናኘ መሆኑን ሲያረጋግጥ፤

ንብረቱ እንዲወረስ ይወስናል፡፡

፪/ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሰረት ከወንጀል ጋር የተገናኘ ንብረት እንዲወረስ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት በንብረቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ ለሚል ማንኛውም ሰው የመሰማት እድል መስጠት አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የተወረሰው ንብረት በዚህ አዋጅ መሰረት ወደ ተቋቋመው ፈንድ ገቢ ይደረጋል፡፡

## ፳፪. የንብረት አስተዳደሪ ስለመሾም

፩/ ፍርድ ቤት ከወንጀሉ ጋር የተገናኘውን ንብረት ወደ ፈንዱ ገቢ እንዲሆን ከመወሰኑ በፊት፡-

ሀ) ንብረቱን የሚያስተዳድር አስተዳዳሪ መሾም፣

ለ) ንብረቱን በይዞታው ወይም በአደራ አስቀማጭነት ወይም በጠባቂነት የያዘን ሰው ንብረቱን እንዲያስረክብ ለማዘዝ፣

7/ For the implementation of this Article, "seizure" shall mean the administration of frozen property by administrator appointed and supervised by a court.

## 21. Confiscation of Property

1/ The court having the jurisdiction to entertain criminal cases indicated under this Proclamation shall order the confiscation of properties associated with the crime:-

a) where it finds the accused guilty of the offence; or

b) though rendering verdict of guilty is impossible due to the offender has been not known, disappeared, dead, or the investigation or prosecution has been suspended for any reason or due to any other reason, if it is ascertained that the property has association with the offence.

2/ The court shall, prior to issuing an order for confiscation of property associated with the crime pursuant to this Article, give an opportunity to be heard to persons who claims that he has a right or interest in the property.

3/ Property confiscated pursuant to this Article shall be awarded to the fund established in accordance with the provisions of this Proclamation.

## 22. Appointment of Property Administrator

1/ The court may, before awarding the property associated with the crime to the fund,

a) appoint administrator to the property;

b) order a person in possession or trustee or care taker of the property to give the property;

www.chilot.me

ሐ) አስተዳዳሪው ንብረቱን በይዞታው ስር እንዲያደርግ፣እንዲጠብቅና እንዲያስተዳድር ለማዘዝ፤

መ) አስተዳዳሪው በአስተዳዳሪነት የተሾመበትን ንብረት ለመጠበቅ፣ ለማስተዳደር እና ለማሻሻል የሚያስችለውን ስልጣን ለመስጠት፤

ሠ) ንብረት አስተዳዳሪው በአስተዳዳሪነት የተሾመበትን ንብረት በተመለከተ የመክሰስና መከሰስ መብት እንዲኖረው፤ ከንብረቱ የሚገኝ ኪራይ፣ ትርፍ ወይም ሌላ ማንኛውንም ገቢ ለመሰብሰብ እና የሰበሰበውንም ገንዘብ ንብረቱን ለማስተዳደር ጠቃሚ ለሚሆን ጉዳይ ለማዋል እንዲችል ወይም ተገቢ መስሎ የታየውን ሌላ ስልጣን ለመስጠት፤

ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሰረት ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ትእዛዝ ንብረቱን ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን ወጪ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውም ሹመቱን ከመስጠቱ በፊት የሂሳብ ማጣራት እንዲደረግ ለማዘዝ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በአስተዳዳሪነት የሚሾመው የተፈጥሮ ሰው የሆነ እንደሆነ መልካም ሥነ-ምግባርና ችሎታ ያለው፣ በንብረቱ ላይ የጥቅም ግጭት የሌለው፣ ከተከሳሽ ወይም በንብረቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም ካለው ሰው ጋር ዝምድና ወይም የጥቅም ግንኙነት የሌለው መሆን ይኖርበታል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በአስተዳዳሪነት የሚሾመው የህግ ሰውነት ያለው ድርጅት ከሆነ፤ ድርጅቱ ባለፉት ሶስት

c) order the administrator to take in his possession, protect and administer the property;

d) give powers that enable the administrator to protect, administrate and improve the property he was appointed as administrator;

e) entrust the administrator with the powers to sue and be sued regarding the property he was assigned as administrator; to collect the rents, profits or other incomes from the property, to use the proceeds for matters useful to the administration of the property, or any other powers the court considers appropriate.

2/ The orders given by the court in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall take into account the expenses necessary for the administration of the properties. Where the court finds it necessary, it may also order an Audit prior to the appointment of the administrator.

3/ Where the administrator appointed in accordance with Sub-Article (1) of this Article is a natural person, he should be of good conduct and have the necessary capabilities, have no conflict of interest in the property, have no relationship with the accused or anyone who have claim of right or interest against the property.

4/ Where the administrator appointed in accordance with Sub-Article (1) of this Article is an organization with legal

www.chilot.me

ዓመታት የኦዲት ግኝት የሌለበት፣ መልካም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ያለው መሆኑን እና የጥቅም ግጭት የሌለው መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ንብረት አስተዳዳሪን ፍርድ ቤት የሚሾመው በራሱ ተነሳሽነት፣ በፖሊስ ወይም በዐቃቤ ህጉ አመልካችነት ሊሆን ይችላል፡፡

## ክፍል አራት
## ስለተጎጂዎች ጥበቃ፣ መልሶ ማቋቋም እና ካሣ

### ፳፫. ተጎጂዎችን ስለመመለስ

፩/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አግባብነት ካላቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር በውጭ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተጎጂዎችን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፪/ ተጎጂው የታሰረ ወይም የተያዘ እንደሆነ ተጎጂው ባለበት አገር የሚገኝ ወይም በቅርበት የሚሰራ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተጎጂው እንዲለቀቅ እና ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ የሚቻለውን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡

፫/ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በየደረጃው ያሉ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ መስሪያ ቤቶች አግባብነት ካላቸው መንግሥታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር በሀገር ውስጥ የሚገኙ እንዲሁም ከወጪ አገር የተመለሱ ተጎጂዎችን እንዳሉበት ነባራዊ ሁኔታ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ ወደ አካባቢያቸው እንዲመለሱ ያደርጋሉ፡፡

personality; it has to be proved that the organization has no Audit fault within the past three years, has good financial system and no conflict of interest.

5/ The court appoints an administrator in accordance with this Article at its own initiative or upon application by the police or public persecutor.

## SECTION FOUR
## PROTECTION OF VICTIM, REHABILITATION AND COMPENSATION

### 23. Returning Victims

1/ The Ministry of Foreign Affairs shall have the responsibility, in collaboration with the appropriate governmental and non-governmental organizations, to repatriate to Ethiopia victims who are Ethiopian nationals found in foreign countries.

2/ Where the victim has been detained or arrested in foreign country, the Ethiopian diplomatic mission in the country the victim located or works close to the location shall, in collaboration with concerned bodies, exert all possible efforts to have the victim released and repatriated to Ethiopia.

3/ Ministry of Labor and Social Affairs and the labor and social affairs offices at all levels shall, in collaboration with the appropriate governmental and non-governmental organizations, return victims located within the country by providing the necessary support as the situation they hold as well as repatriated from abroad to their respective localities.

www.chilot.me

፬/ ስለቪዛ፣ ስለጉዞ ሰነድ እና ሌሎች ሁኔታዎች በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ተጎጂ በኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘ እንደሆነ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት እና ከሚመለከተው አገር ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ጋር በመተባበር ተጎጂው ወደ አገሩ እንዲመለስ ያደርጋል፡፡

## ፳፬. <u>የተጎጂዎች ጥበቃ እና መልሶ ማቋቋም</u>

፩/ ተጎጂዎች፡-

ሀ) አስፈላጊው ጥበቃ እና ድጋፍ ይደረግላቸዋል፣ የሚደረገው ጥበቃ እና ድጋፍ የተጎጂዎቹን ሁኔታ ያማከለ በተለይም የሴቶች፣ ህጻናት፣ የአዕምሮ ህመምተኛ እና አካል ጉዳተኞችን ለአደጋ ተጋላጭነትና ልዩ ፍላጎት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፣

ለ) ግላዊ ሚስጥራቸውን እና ሰብዓዊ ክብራቸውን በጠበቀ መልኩ መያዝ እና ተገቢው የጤና፣ የማህበራዊ አገልግሎት፣ የህግና ሥነ-ልቦና ምክርና ድጋፍ፣ ጊዜያዊ መጠለያ እና መሰል አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ይደረጋል፣

ሐ) ስለሚደረግላቸው ጥበቃና ድጋፍ፣ እና በምርመራና በፍርድ ሂደት ወቅት ጉዳዩ ስለደረሰበት ደረጃ መረጃ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

መ) በማንኛውም ሁኔታ በፖሊስ ጣቢያ፣ በማረፊያ ቤት ወይም በማረሚያ ቤት እንዲቆዩ መደረግ የለባቸውም፡፡

4/ Without prejudice to the provisions of other laws on visa, travel documents and other matters, where a victim who is a foreign national found in Ethiopia, the Ministry of Foreign Affairs shall, in collaboration with the appropriate bodies and the diplomatic mission of the concerned country, facilitate the repatriation of the victim to his country of origin.

## 24. <u>Protection and Rehabilitation of Victims</u>

1/ Victims shall:-

a) receive the necessary protection and support; the protection and support accorded shall be in consideration of the victims situation, particularly shall take in to account the vulnerability and special needs of women, children, person with mental problem and disabilities.

b) be treated in a manner protective of their privacy and dignity and provided appropriate health, social services, legal and psychological counseling and support, temporary shelter, and other similar services.

c) have the right to information on the nature of protection and support to be accorded, and status of the case during investigation and prosecution.

d) not be placed in a police station, detention center or prison facility under any circumstances.

www.chilot.me

፪/ የተጎጂው ሁኔታ ካላስገደደ ወይም ተጎጂው ለምርመራ ወይም ለክርክር ሂደት አስፈላጊ የሆነና ለመመስከር ፈቃደኛ የሆነ ካልሆነ በስተቀር በጊዜያዊ መጠለያ ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ መደረግ የለበትም፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ወንጀሎችን ለመከላከል፣ ለመመርመር፣ ክስ ለማቅረብ ወይም የዳኝነት ውሳኔ ለመስጠት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ተጎጂን በሚያገኙበት ወቅት የተጎጂውን ሁኔታ ከግምት በማስገባት የተሻለ ድጋፍ እና እንክብካቤ ወደሚያገኝበት ተቋማት ተጎጂውን የመላክ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፬/ የፌደራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ መኖሪያቸው በከተማ ለሆኑ ተጎጅዎች መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊውን የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፭/ የገጠር የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ መኖሪያቸው በገጠር ለሆኑ ተጎጅዎች መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊውን የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፮/ ስለስደተኞች በሌላ ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ የሌለው የውጭ አገር ዜጋ ተጎጂ ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘ እንደሆነ ተጎጂዎች በኢኮኖሚ እራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ ከሚፈፀመው የመልሶ ማቋቋም አገልግሎት በስተቀር ተገቢው ድጋፍ ይደረግለታል፡፡ እንደነገሩ ሁኔታም ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ እንዲያገኝ ሊደረግ ይችላል፡፡

2/ Unless the situation of the victim so compels or the presence of the victim is necessary for the trial process and the victim is willing to give testimony, the victim shall not be placed in a temporary shelter for an extended period.

3/ The Authorities entrusted with power to prevent, investigate, prosecute or give judicial proceeding regarding crimes stipulated under this Proclamation shall have the responsibility to refer victim in contact, taking in to account situation of the victim, to an institution where the victim can get better support and care.

4/ The Federal Urban Employment Creation and Food Security Agency, in collaboration with the appropriate governmental and non-governmental bodies, provide necessary rehabilitation support to victims residing in urban areas.

5/ The Rural Employment Creation and Food Security Agency in collaboration with the appropriate governmental and non-governmental bodies, provide necessary rehabilitation support to victims residing in rural areas.

6/ Without prejudice to the provisions regarding refugees provided in other laws, where a victim who is a foreign national found in Ethiopia not having permanent residence permit shall receive the appropriate support with the exception victims economic empowerment rehabilitation service. He may also, as appropriate, be provided with a temporary residence permit.

www.chilot.me

**፳፭. <u>የምስክሮች ጥበቃ</u>**

በዚህ አዋጅ በተመለከተ ወንጀል ምስክር ወይም ጠቋሚ የሆነ ሰው በዚሁ ምክንያት የእርሱ ወይም የቤተሰቡ ሕይወት ወይም ንብረት ለአደጋ የተጋለጠ እንደሆነ በምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፱/፪ሺ፫ መሰረት ተገቢ ጥበቃ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

**፳፮. <u>ስለካሣ</u>**

፩/ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ በተመለከተው ወንጀል በተከሳሽ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ በመስጠት ከሚወስነው ቅጣትና መቀጮ በተጨማሪ የሕክምና፣ የትራንስፖርት እና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው ወጪዎችን ጨምሮ ተጎጂው ላይ ለደረሰው የጉዳት ካሳ እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ተጎጂውን ለማዳንና ለመንከባከብ ያወጡትን ወጪ እንዲከፈል ሊወስን ይችላል፡፡

፪/ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ በተመለከተ ወንጀል ምክንያት የህሊና ጉዳት ለደረሰበት ሰው ከአንድ ሺህ እስከ ሃምሳ ሺህ ብር የሚደርስ የህሊና ጉዳት ካሳ ለመወሰን ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚወሰን ካሳ በማናቸውም ሁኔታ ተጎጂው ለወንጀል ፈፃሚው ከከፈለው ገንዘብ፣ ካስገኘው ጥቅም ወይም በወንጀል ድርጊቱ ምክንያት ተጎጂው ካጣው ወይም ሊያጣው ከሚችለው ገቢ ያነሰ መሆን የለበትም፡፡

፬/ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ወይም በዐቃቤ ህግ አመልካችነት የካሳ ጉዳይን ከወንጀል መዝገቡ ጋር በማጣመር ወይም ከወንጀል መዝገቡ በመነጠል ለማየት ይችላል፡፡

**25. <u>Protection of Witnesses</u>**

Where the life or property of any person or his family is endangered for being a witness or whistleblower of an offence stipulated under this proclamation, protection shall be given in accordance with the protection of Witnesses and Whistleblowers of Criminal Offences Proclamation No.699/2010.

**26. <u>Compensation</u>**

1/ The court may, in addition to the fines and penalties imposed upon passing verdict of guilty for offences stipulated under this proclamation, award compensation to the victim for harm suffered including medical, transport and other relevant cost incurred by the victim as well as by other parties to rescue and care the victim.

2/ The court may award compensation of moral damages from One Thousand to Fifty Thousand Birr for victims suffered moral damage for reason of commission of crimes stipulated under this Proclamation.

3/ The compensation to be awarded in accordance with this Article may not under any circumstances be less than the amount paid by the victim to the perpetrator, income gained by the act or income lost or future lose by the victim due to the offence committed.

4/ The court may entertain the issue of compensation together with or as separate from the criminal file by its own initiation or application of public prosecutor.

www.chilot.me

፭/ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ መሰረት ካሳን የወሰነ እና ተከሳሽ መክፈል የማይችል መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ለተጎጂው ወይም ስለተጎጂው ወጪ ላወጡ ሌሎች ሰዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በተመለከተው መጠንና ሁኔታ መሰረት ከፈንዱ እንዲከፈል ሊወስን ይችላል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት ፍርድ ቤት ከፈንዱ እንዲከፈለው የወሰነው የካሳ መጠን ለተጎጂው የወሰነው አጠቃላይ ካሳ መጠን ያልሆነ እንደሆነ፤ ቀሪውን የጉዳት ካሳ ተጎጂው የድርጊቱ ፈፃሚ የመክፈል አቅም ሲኖረው ለመጠየቅ ይችላል፡፡ መንግስትም ከፈንዱ ለተጎጂው ለከፈለው መጠን ተከሳሽን ለመጠየቅ ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት
## ስለፈንድ መቋቋም

**፳፯. መቋቋም**

በሰው የመነገድ፣ በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር እና በህገ ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ አገር መላክ ወንጀል ተጎጂዎችን መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ (ከዚህ በኋላ “ፈንድ” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**፳፰. የገቢ ምንጭ**

የፈንዱ የገቢ ምንጭ፡-

፩/ ከመንግስት ከሚመደብ በጀት፣

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወረሱ ንብረቶችና የሚሰበሰቡ መቀጮዎች፣

፫/ ከግለሰቦች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ከሚገኝ ልገሳ እና እርዳታ፣ እና

፬/ ከሌሎች የገንዘብ ሚኒስቴር ከሚያፀድቃቸው የገንዘብ ምንጮች ከሚገኙ ገቢዎች፣

ይሆናል፡፡

5/ Where the court has rewarded compensation to the victim in accordance with this Article and ascertained that the accused is incapable to cover it, the court may, in accordance with amount and condition set by the Regulations to be issued by the Council of Ministers, order that the compensation and expenses be paid from the fund for the victim and other parties incurred cost on behalf of the victim.

6/ Where payment made from fund in accordance with Sub-Article (5) of this Article is not in full amount of compensation, the victim may demand payment of the difference from the accused when he is capable to pay. The state also may demand reimbursement for payments made from the fund to the victim.

## SECTION FIVE
## ESTABLISHMENT OF FUND

**27. Establishment**

A fund for the rehabilitation of victims of crime of trafficking in persons, the smuggling of persons and unlawful sending of person abroad for work (hereinafter “the Fund”) has been established under the provisions of this Proclamation.

**28. Sources of Income**

The source of income for the Fund shall be:-

1/ budget allocated by the government;

2/ properties confiscated and fines collected in accordance with this Proclamation;

3/ grants and aids from individuals, governmental and non-government organizations; and

4/ other sources of income to be approved by the Ministry of Finance.

www.chilot.me

**፳፱. ዓላማ**

የፈንዱ ዓላማ፦

፩/ የተጎጂዎች የህክምና፣ የሥነ-ልቦናና የህግ ምክር፣ የትራንስፖርት እና መሰል አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ የሚወጣ ወጪን ለመሸፍን፤

፪/ ለተጎጂዎች ቁሳዊ እርዳታን ለማድረግ፤

፫/ ለተጎጂዎች የሙያ ሥልጠና እና በኢኮኖሚ እራሳቸውን እንዲችሉ ድጋፍ ለማድረግ፤

፬/ የተጎጂዎችን ቤተሰብ ማፈላለግ እና ከቤተሰብና ከማሕበረሰቡ ጋር ለማቀላቀል የሚደረገውን ጥረት ድጋፍ ለማድረግ፤

፭/ ለተጎጂዎች ጊዜያዊ መጠለያ ግንባታን ለማከናወን፤ እና

፮/ በፍርድ ቤት የሚወሰን ካሳን በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሰረት ለመክፈል፤

ነው፡፡

**፴. የፈንዱ አስተዳደር እና አጠቃቀም**

ፈንዱ ስለሚተዳደርበት፣ ለተጎጂዎች አገልግሎት ስለሚውልበት፣ ፍርድ ቤት ለተጎጂዎች ካሳ ከፈንዱ እንዲከፈላቸው ስለሚወስንበት ሁኔታና መጠን እና ተያያዥ ጉዳዮች ስለሚፈፀሙበት አግባብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**፴፩. የፈንዱ የሂሳብ መዝገብና ኦዲት**

፩/ የፈንዱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

፪/ ፈንዱን የሚያስተዳድረው አካል የኦዲት ሪፖርቱን የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ተጠሪ ለሆነለት አካል ማቅረብ አለበት፡፡

**29. Objective**

The objective of the Fund shall be:

1/ to cover the costs of medical, psychological and legal counsel, transportation and other services for victims;

2/ to provide material support to victims;

3/ to provide technical training and support for the economic empowerment of victims;

4/ to provide support for an effort to locate families and reintegrate victims with their families and communities;

5/ for the construction of temporary shelters to victims; and

6/ to pay compensation determined by the court in accordance with Regulations to be issued by the Council of Ministers.

**30. Administration and Utilization of the Fund**

The manner of the administration of the fund, utilization in providing service to victims, amount and conditions a court orders compensation to be paid from the fund and other related matters shall be determined by Regulations to be issued by the Council of Ministers.

**31. The Accounts and Audits of the Fund**

1/ The books of accounts and other financial records of the Fund shall be audited annually by the Auditor General or by the Auditor assigned by the Auditor General.

2/ The body responsible for the administration of the Fund shall submit an Audit report to the body to whom it is accountable within four months following the end of the budget year.

www.chilot.me

## ፴፪. የበጀት ዓመት

የፈንዱ የበጀት ዓመት የመንግስት የበጀት ዓመት ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ስለብሔራዊ ምክር ቤት፣ የተቋማት ሚና እና ትብብር

## ፴፫. ስለብሔራዊ ምክር ቤት መቋቋም

፩/ በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና በህገ ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ መላክ ወንጀል መከላከልና መቆጣጠር በብሔራዊ ደረጃ አስተባባሪ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ብሔራዊ ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የብሔራዊ ምክር ቤቱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

፫/ ብሔራዊ ምክር ቤቱ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ ሆኖ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የሰላም ሚኒስቴር፣ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ፣ የሴቶች፣ሕጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር፣ የስራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽን፣ የጤና ሚኒስቴር፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የብሔራዊ ባንክ፣ የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ፣ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ፣ ክልሎች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ እና እንደ አግባብነቱ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲካተቱ የሚደረጉ ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን ያቀፈ ይሆናል፡፡

፬/ የብሔራዊ ምክር ቤቱ አባላት በተቋማቱ ኃላፊዎች ወይም ምክትል ኃላፊዎች የሚወከሉ ይሆናል፡፡

## 32. Budget Year

The budget year of the Fund shall be the budget year of the Government.

## SECTION SIX
## THE NATIONAL COUNCIL, INSTITUTIONAL ROLES AND COOPERATION

## 33. Establishment of the National Council

1/ A Council at national level to coordinate the prevention and control of the crimes of trafficking in persons, smuggling of persons and unlawful sending of person abroad for work (hereinafter "the National Council") is hereby established under this Proclamation.

2/ The National Council shall be accountable to the Prime Minister.

3/ The National Council shall be chaired by the Deputy Prime Minister and shall composes the Federal Attorney General, the Ministry of Foreign Affairs, the Ministry of Peace, the Ministry of Labor and Social Affairs, the Refugees and Returnees Affairs Agency, the Ministry of Women's, Children's and Youth Affairs, the Commission of Job Creation, the Ministry of Health, the Federal Police Commission, the National Bank, the Central Statistics Agency, the National Intelligence and Security Services, Regional Governments, the Civil Societies Agency, Religious Institutions, and other concerned bodies to be nominated by the Deputy Prime Minister.

4/ Members of the National Council shall be represented either by the Head or Deputy of the Organization.

www.chilot.me

፭/ ክልሎች አግባብነት ያላቸውን የክልሉ ተቋማትን ያቀፈና ተጠሪነቱ ለክልሉ ፕሬዚዳንት የሆነ መሰል ምክር ቤት ሊኖራቸው ይችላል፡፡

## ፴፬. የብሔራዊ ምክር ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት

ብሔራዊ ምክር ቤቱ፡-

፩/ በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና በህገ ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ አገር መላክ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ፖሊሲ፣ ሕግ እና ስትራቴጂ ያመነጫል፤ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ በሌላ ሕግ በግልፅ ፖሊሲ፣ ሕግ እና ስትራቴጂ እንዲያመነጭ ስልጣን የተሰጠው አካል ሲኖር ያስተባብራል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፪/ ተጎጂዎችን ማዳን፣ መልሶ ማቋቋም፣ ልዩ ልዩ ድጋፍ ስለሚያገኙበት ሁኔታ፣ ከህብረተሰቡ ጋር ሊቀላቀሉ ስለሚችሉበት እና ተያያዥ ጉዳዮችን የተመለከተ አገር አቀፍ የቅብብሎሽ ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፤

፫/ ስለአገር ውስጥ መፈናቀል፣ ስደት እና ፍልሰት በህግ ተግባርና ኃላፊነት የተሰጣቸውን አካላት በማስተባበር የፖሊሲ፣ የሕግ ወይም ስትራቴጂ ማዕቀፍ እንዲወጣ ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፬/ ለስደትና ፍልሰት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍና ምላሽ ስለሚደረግበት፣ የስራ ዕድል ስለሚፈጠርበትና መሰል ጉዳዮች ተግባራዊ ስለሚደረጉበት ሁኔታ ምክረ-ሀሳብ ያቀርባል፣ እነዚህን ጉዳዮች ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት ያለባቸው ተቋሞች ተግባራቸውን ስለመፈፀማቸው ይከታተላል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

5/ Regional States may establish similar council composed of relevant institutions of the region which is accountable to the president of the region.

## 34. Function and Responsibilities of the National Council

The National Council shall:-

1/ initiate policies, laws and strategies for the prevention and control of the crimes of trafficking in persons, smuggling of persons and unlawful sending of person abroad for work; coordinate, if there are, bodies clearly mandated to initiate policies, laws and strategies on these matters and follow ups implementation upon approval;

2/ issue a Directive for the creation of a national referral mechanism for the rescue, rehabilitation, provision of support, reintegration of victims and other related matters;

3/ coordinate, for initiation of policy, law or strategy, organs entrusted with function and responsibilities related to matters of internal displacement, refuge or migration; follow up its implementation.

4/ provide recommendation as to providing support and response to section of the society vulnerable to refuge and migration, job creation and other related matter manners of implementation; follow up the execution of these matters by the organs mandated to and provide appropriate assistance;

www.chilot.me

፭/ ለብሔራዊ የትብብር ጥምረት የሥራ መመሪያ ይሰጣል፣ የጥምረቱን መርሀ ግብር ያፀድቃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ጉድለቶች እንዲስተካከሉ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

፮/ የውስጥ አሰራሩን እና ከብሔራዊ አስተባባሪ ጥምረቱ ጋር ስለሚኖረው የአሰራር ግንኙነት በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፡፡

**፴፭. ስለብሔራዊ አስተባባሪ ጥምረት መቋቋም**

፩/ በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና በህገ ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ አገር መላክ ወንጀሎች ተከላካይ ብሔራዊ የትብብር ጥምረት (ከዚህ በኋላ "ብሔራዊ የትብብር ጥምረት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ ተጠሪነት ለብሔራዊ ምክር ቤቱ ይሆናል፡፡

፫/ ጥምረቱ በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የሚመራ ሆኖ ክልሎችን ሳይጨምር በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፴፫ (፫) ላይ የተመለከቱትን አካላት ያካተተ ይሆናል፡፡

፬/ የብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ የውስጥ አደረጃጀት እና አሰራር ብሔራዊ ምክር ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፭/ ክልሎች ይህን ህግ ለማስፈፀም እንደየክልሉ ነባራዊ ሁኔታ አግባብነት ያላቸውን አካላት ያቀፈ እና በዐቃቤ ህግ ተቋም የሚመራ የክልል የትብብር ጥምረት ማቋቋም አለባቸው፡፡

**፴፮. የብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ ተግባርና ኃላፊነት**

የብሔራዊ የትብብር ጥምረት፡-

5/ give operational guide to the National Partnership Coalition, approve programs and action plan of the coalition, follow up on its implementation and provide redress for gaps.

6/ issue Directives regarding its internal working procedures and relationship with the National Partnership Coalition.

**35. Establishment of the National Partnership Coalition**

1/ A National Partnership Coalition for the Prevention of the crimes of trafficking in persons, smuggling of persons and unlawful sending of person abroad for work (hereinafter "the National Partnership Coalition") is hereby established under this proclamation.

2/ The National Partnership Coalition shall be accountable to the National Council.

3/ The National Partnership Coalition to be chaired by the Federal Attorney General, shall incorporates, with the exclusion of Regional States, the bodies listed under Article 33 (3) of this Proclamation.

4/ The internal structure and working procedures of the National Partnership Council shall be determined by a Directive to be issued by the National Council.

5/ The Regional States, to implement this law, shall establish Regional Partnership Coalitions incorporating bodies relevant to their respective context and to be led by the justice bureaus.

**36. Function and Responsibilities of the National Partnership Coalition**

The National Partnership Coalition shall:

www.chilot.me

፩/ በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና በህገ ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ አገር መላክ ወንጀሎችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ተጎጂዎችን መልሶ ለማቋቋም የሚያስችሉ ጥናቶችን በማጥናት፣ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ህጎችን በማዘጋጀት ለብሔራዊ ምክር ቤቱ ያቀርባል፤ አግባብ ባለው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ያስተባብራል፤

፪/ ተጎጂዎችን ማዳን፣ መልሶ ማቋቋም፣ ልዩ ልዩ ድጋፍ ስለሚያገኙበት ሁኔታ፣ ከህብረተሰቡ ጋር ሊቀላቀሉ ስለሚችሉበት እና ተያያዥ ጉዳዮችን የተመለከተ አገር አቀፍ የቅብብሎሽ ሥርዓት መመሪያ እና የአሰራር ሥርዓት ያዘጋጃል፤ በብሔራዊ ምክር ቤቱ ሲፀድቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

፫/ ስለአገር ውስጥ መፈናቀል፣ ስደትና ፍልሰት፣ የስራ ዕድል ፈጠራና መሰል ጉዳዮችን የተመለከተ የፖሊሲ፣ የህግ ወይም የስትራቴጂ ማዕቀፍ እና የአሰራር ሥርዓት እንዲዘጋጅ የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፬/ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ተግባራዊ ለማድረግ ዕቅድና የድርጊት መርሐ-ግብር ያዘጋጃል፤ ለብሔራዊ ምክር ቤቱ በማቅረብ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮች ተግባርና ኃላፊነት በተናጠል የተሰጣቸው ተቋማት ተግባርና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ስለመወጣታቸው ይከታተላል፣ አፈጻጸሙን ለብሔራዊ ምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡

፮/ ለብሔራዊ ምክር ቤቱ በየወቅቱ ሪፖርት ያቀርባል፣ የሚሰጡ ግብረ መልሶችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

1/ submit to the National Council by undertaking research and preparing policies, strategies and laws that enables the prevention and control of the crimes of trafficking in persons, smuggling of persons and unlawful sending of person abroad for work and the rehabilitation of victims; coordinate the implementation upon approval by the appropriate body.

2/ develop directives of national referral system and implementation procedure, regarding rescuing, rehabilitation, provision of support, reintegration of victims and other related matters; coordinate implementation of the same upon approval by the National Council.

3/ coordinate concerned bodies for the development of policies, laws and strategies frameworks and implementation procedures regarding internal displacement, refuges and migrations, job creation and other related matters; follow up implementation up on approval by concerned body.

4/ prepare program and action plan for realization of its functions and responsibilities; implement up on submission and approval by the National Council.

5/ follow up institutions unilaterally entrusted with function and responsibilities related with matters covered by this Proclamation as to their proper execution of such function and responsibilities.

6/ periodically submit report to the National Council; implement given feedbacks.

www.chilot.me

፯/ በአዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰ አንቀጽ ፲፭ (፪) የተመለከተውን ተግባራት ያከናውናል፤

፰/ ሌሎች በብሔራዊ ኮሚቴው የሚሰጡ ልዩ ልዩ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፴፯. <u>ስለጥምረቱ ጽህፈት ቤት</u>**

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ ተግባርና ኃላፊነቱን እንዲወጣ የሚደግፍና የሚያስተባብር ጽህፈት ቤት ያደራጃል፡፡

፪/ የክልል ዐቃቤ ህግ ተቋማት የክልል የትብብር ጥምረትን የሚደግፍና የሚያስተባበር ጽ/ቤት ያደራጃሉ፡፡

**፴፰. <u>የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ኃላፊነት</u>**

በሌላ ህግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ:-

፩/ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ወንጀሎች ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሕግ አስከባሪ አካላትን ሚና፣ ወንጀሉን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጡ ህጎችን፣ወንጀለኞች ስለሚጠቀሟቸው የመመልመያ ዘዴዎች፣ ስለብዝበዛ ዓይነቶች እና የአፈጻጸም ስልቶች እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮችን አስመልክቶ ለህብረተሰቡና ለሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ ይፈጥራል፤

፪/ ለፌደራልና ክልል ፖሊስ፣ ዐቃቤያነ ህግና ዳኞች የወንጀል መከላከል፣ የምርመራ ስራዎችን፣ ማስረጃ ምዘናን እና ተያያዥ ጉዳዮችን አስመልክቶ የአቅም ግንባታ ስራ ያከናውናል፡፡

7/ undertake the responsibilities indicated under Article 15(2) of Proclamation Number 923/2016.

8/ Perform other responsibilities allocated to it by the National Council.

**37. <u>Secretariat of the Coalition</u>**

1/ The Federal Attorney General shall organize a secretariat office that support and coordinate the National Partnership Coalition for undertaking its function and responsibilities.

2/ The Regional Public Prosecutor Offices shall organize a secretariat office that support and coordinate the respective Regional Partnership Coalition.

**38. <u>Responsibilities of the Federal Attorney General</u>**

Without prejudice to the powers and duties assigned to it under other laws, the Federal Attorney General shall፡

1/ create awareness to the public and concerned bodies as to the responsibilities of law enforcement bodies, laws promulgated to prevent and control the crimes, the means of recruitment employed by criminals, the types and means of exploitation and other related matters to prevent and control crimes stipulated under this Proclamation;

2/ undertake capacity building activities regarding the crime prevention, investigation, evidence scrutiny and related matters for Federal and Regional police, prosecutors and judges.

www.chilot.me

**፴፱. <u>የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊነት</u>**

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡-

፩/ ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በውጪ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተጎጂዎችን መረጃ፣ የሚገኙበትን አገር፣ ያሉበትን ሁኔታ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን አስመልክቶ መረጃ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያደርሳል፤

፪/ በውጪ ሀገር የሚገኙ የተለዩ ተጎጂዎችን ወደ ሀገር ቤት እንዲገቡ በማድረግ ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያስረክባል፤

፫/ በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር እና በህገ ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ አገር መላክ ወንጀል መዳረሻ በሆኑ አገራት ለሚገኙ ዜጎች የየአገራቱን የስጋት ደረጃ በመለየት በየወቅቱ በተለያዩ የግንኙነት ዘዴዎች እንዲያውቁት ያደርጋል፤ የየራሳቸውን ማህበረሰብ እንዲያቋቁሙ፣ በማህበረሰቡ አደረጃጀት መሠረት በየአገራቱ መብትና ጥቅማቸው እንዲከበር አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

**፵. <u>የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊነት</u>**

የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከፌደራልና ክልል ፖሊስ፣ ከክልል የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ተቋማት እና ሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር በሀገር ውስጥ የሚገኙ ተጎጂዎችን መረጃ፣ ያሉበትን ሁኔታ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን አስመልክቶ መረጃ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያደርሳል፤ በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ ስልቶችን

**39. <u>Responsibilities of the Ministry of Foreign Affairs</u>**

The Ministry of Foreign Affairs shall:

1/ organize and disseminate, in collaboration with the National Intelligence and Security Service, Ministry of Labor and Social Affairs and other relevant bodies, the data, country they are found, conditions they are in and other related issues of victims who are Ethiopian nationals living in foreign country;

2/ cause the return of victims found in foreign country and transfer them to the Ministry of Labor and Social Affairs;

3/ communicate periodically, using through various means, to victims residing in destination countries of crime of trafficking in persons, smuggling of persons and unlawful sending of person for work abroad as to the level of the risks in respective countries; provide the necessary support for the establishment of communities and for the protection of their rights and interests in the respective countries.

**40. <u>Responsibilities of the Ministry of Labor and Social Affairs</u>**

The Ministry of Labor and Social Affairs shall organize, in collaboration with the Federal and Regional Police, Regional Labor and Social Affairs Bureaus and other institutions, data of victims found in the country as to their current location, the conditions they are in and other relevant matters and disseminate to relevant bodies; in addition, the Ministry in collaboration with concerned governmental and

www.chilot.me

በመጠቀም ለህብረተሰቡ በሰዎች ስለመነገድ እና ሰዎችን በህገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል አስከፊነት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ይሰራል

**፵፩. <u>የፌደራል ፖሊስ ኃላፊነት</u>**

የፌደራል ፖሊስ ከፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፣ ከብሔራዊ መረጃ ደህንነት አገልግሎት፣ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ወንጀሎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እንደነገሩ ሁኔታ በምርመራ፣ መረጃ በመለዋወጥ፣ በአቅም ግንባታ እና በመሳሰሉ ጉዳዮች በጋራ ይሰራል፡፡

**፵፪. <u>የዳኝነት ሥልጣን</u>**

፩/ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ (፪) እና አንቀጽ ፰ (፫) የተመለከቱት ጉዳዮች የሚታዩት ሶስት ዳኛ በተሰየመበት ችሎት ይሆናል፡፡

**፵፫. <u>የዓለም አቀፍ ትብብር</u>**

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ወንጀሎች ምርመራ፣ ወንጀለኛ አሳልፎ መስጠትን፣ መረጃ ልውውጥ እና ሌሎች የጋራ ትብብር የህግ ድጋፍ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከሌላ ሀገር አግባብ ካለው ባለሥልጣን ጋር እንካ በእንካ መርህን፣ ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን በሆነችበት ስምምነት እና የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት በሚፈቅደው መሠረት በትብብር ይሰራል፣ እንዲሁም ማዕከላዊ ባለስልጣን ሆኖ ያገለግላል፡፡

non governmental bodies creat awareness to the society on bad feature of trafficking in person and smuggling of persons.

**41. <u>Responsibilities of the Federal Police</u>**

The Federal Police shall work, as the case may be in investigation, information exchange, capacity building and similar matters, in collaboration with the Federal Attorney General, National Security and Intelligence Service, Ministry of Labor and Social Affairs and other stakeholders to prevent and control the crimes stipulated under this Proclamation,.

**42. <u>Judicial Powers</u>**

1/ The Federal First Instance Court shall have first instance jurisdiction over matters stipulated under the provisions of this Proclamation.

2/ Cases involving matters stipulated under Article 4 (2) and Article 8(3) of this Proclamation shall be tried in a bench presided by three judges.

**43. <u>International Cooperation</u>**

1/ The Federal Attorney General:-

a) shall cooperate with the competent authority of another country in the investigation, extradition of criminals, exchange information and mutual legal cooperation in relation to crimes stipulated under this proclamation based on the principle of reciprocity, agreements to which Ethiopia is a party and in line with the country's legal system; and serves as a central authority.

www.chilot.me

ለ) እንደአስፈላጊነቱ ወንጀሎቹን ለመከላከል እና ተጠርጣሪዎችን ለፍርድ ለማቅረብ የሚያስችሉ ስምምነቶችን ከሌሎች አገራት ጋር ልዩ ልዩ የትብብር ማዕቀፎችን ሊፈራረም ይችላል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ የፌደራል ፖሊስ ተመሳሳይ ተልዕኮ ካለው መሰል የሌላ ሀገር ተቋም ጋር በህግ ተቋሙ ከተሰጠው ስልጣን ጋር በተያያዘ እንካ በእንካ መርህ እና በኢትዮጵያ የህግ ማዕቀፍ መሰረት የመረጃ ልውውጥና የጋራ ትብብር ሊያደርግ እና የመግባቢያ ስምምነት ለመፈራረም ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፵፬. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩/ ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች ይህ አዋጅ ለተከሳሽ የተሻለ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፱/፪ሺ፯ ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት ፍፃሜ ያገኛሉ፡፡

፪/ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና የሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፱፻፱/፪ሺ፯ መሰረት አድርገው የወጡ መመሪያዎች በሌሎች መመሪያዎች እስከሚተኩ ድረስ ከዚህ አዋጅ ጋር በሚጣጣም መልኩ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

### ፵፭. ስለተሻረ እና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ድንጋጌዎች

b) may, as appropriate, sign various cooperation framework agreements with other countries to prevent crimes stipulated under this Proclamation and to bring suspects to justice.

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Federal police may engage in information exchange, mutual cooperation and sign a memorandum of understanding, with regard to mandate given by law to it, with institution of another country which have similar mission based on the principle of reciprocity and legal framework of Ethiopia.

## SECTION SEVEN
## MISCELANEOUS PROVISIONS

### 44. Transitory Provisions

1/ Unless this Proclamation favors the accused person, all pending cases before the coming in to force of this proclamation shall continue to be governed in accordance with the Prevention and Suppression of Trafficking in Persons and Smuggling of Migrants Proclamation No. 909/2015 or other appropriate laws.

2/ Directives enacted in accordance with the provisions of the Prevention and Suppression of Trafficking in Persons and Smuggling of Migrants Proclamation No. 909/2015 shall continue to have effect in a manner consistent with the provisions of this proclamation until replaced by other directives.

### 45. Repealed Laws and Inapplicable provisions

www.chilot.me

፩/ "ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ሰውን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፱/፪ሺ፯" በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፪፻፵፫ (፪)፣ (፫)፣ ከአንቀጽ ፭፻፺፮ እስከ አንቀጽ ፭፻፺፱ እና ከአንቀጽ ፮፻፴፬ እስከ አንቀጽ ፮፻፴፰ የተመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

፫/ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፪፻፵፫(፩) ፊደል ተራ (ለ) እና የኢሚግሬሽን አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፬/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳ (፪) በኢትዮጵያ እንዲቆይ መርዳቱ የተፈፀመው የገንዘብ ወይም ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በሚሆንበት ጊዜ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## ፵፮. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፵፯. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1/ The Prevention and Suppression of Trafficking in Persons and Smuggling of Migrants Proclamation No. 909/2015 is hereby repealed.

2/ The provisions of Article 243 (2) and (3), from Article 596 to Article 599 and from Article 634 to Article 638 of the Criminal Code are hereby repealed.

3/ The provisions of Article 243 (1) (b) of the Criminal Code and Article 20(2) of the Immigration Proclamation Number 354/2003 shall not be applicable where the assistance made to enable stay in Ethiopia is provided for financial or other material benefit.

## 46. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Federal Attorney General may issue Directives necessary for the effective implementation of this Proclamation and Regulations issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

## 47. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa on this 1st Day of April, 2020**

**SAHLEWORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me